ISRAEL NATURE AND PARKS AUTHORITY

የእብድ ውሻ በሽታን ስርጭት መቀነስ - በሁላችንም እጅ ነው።

የእብድ ውሻ በሽታ ለሰው እና ለእንስሳት አደገኛ በሽታ ነው, ስለዚህ አስቸኳይ ህክምና ያስፈልገዋል።
የበሽታው ዋነኛ ተሸካሚዎች ጃክሎች, ቀበሮዎች እና የባዘኑ ውሾች ሲሆኑ በሽታው በተበከለ እንስሳ እና ባልተከተቡ እንስሳት መካከል በሚደረግ ግንኙነት ይተላለፋል. ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለተከሰተው የእብድ ውሻ በሽታ፣ ከእስራኤል ድንበር ውጭ የደረሱ የተጠቁ እንስሳት (ሊባኖን፣ ሶሪያ፣ ዮርዳኖስ) ተጠያቂ ናቸው። የግብርና ሚኒስቴር የእብድ ውሻ በሽታን የመከላከል አደራ ተሰጥቶት በሽታውን ለመግታትና ለማከም መመሪያ ያወጣል። ነገር ግን የበሽታው ተሸካሚዎችም የዱር እንስሳት (በዋነኛነት ጃክሎች) በመሆናቸው የተፈጥሮና ፓርኮች መ/ቤት ባለስልጣን የበሽታውን ስርጭት ለመቋቋም በመታገል ላይ ይገኛል። የበሽታውን ስርጭት መቀነስም በሁላችንም እጅ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

በሽታው በዱር እንስሳት ላይ እንዲስፋፋ የሚያደርገው ምንድን ነው?

ለበሽታው መስፋፋት ዋነኛው ምክንያት በዱር እንስሳት ብዛት ና መጨናነቅ ምክንያት ከተፈጥሮ ውጪ በሆነ የመራባት ምክንያት ነው። ብዛ ታቸዉ እየጨመረ በሄደ መጠን የበሽታ መተላለፍ እድሉ ይጨምራል።:
ለጃክሎች እና ለሌሎች የዱር እንስሳት መብዛት ወሳኙ ነገር አብዛኛው አመቱን በሙሉ በሰው እንቅስቃሴ ምክንያት በየቦታዉ በ ሚገኝ ምግብ ነው። ምግብ በሚገኝበት አካባቢ ብዙ ታዳጊ እንስሳት ወደ ጉልምስና ይደርሳሉ , በዚህም ምክንያት የ እንስሳት ብዛት መጨናነቅ ይፈጠራል . ምግቦች በየቦታው ይገኛሉ በቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ፣ ባልተዘጋጉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ፣ የቤት እንስሳት ምግቦች (ውሾች እና ድመቶች) በእንስሳት እርባታ በደሮ እርባታ ቤቶች ፣ በረቶ ች ፣ የአሳ ማርቢያ እና ሌሎችም ። በተጨማሪም, በቀላሉ ምግ ብ የሚገኘ ባቸ ው ቦታዎች የዱር እንስሳት ን በመሳብ ወደ የ ቤት እንስሳት ና እና ወደ እርሻ እንስሳት, ለታመሙ እንስሳት አደገኛ ተጋላጭነትን ይጨምራል ።

ምን ማድረግ አለብን ?

ተፈጥሮ እና ፓርኮች መ ቤት ባለስልጣን የእብድ ውሻ በሽታን በቁም ነገር የሚመለከት ሲሆን የግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ህክምና አገልግሎትን እና የአካባቢውን ባለስልጣናትን ጨምሮ ሁሉንም ሃላፊነት ከሚወስዱ አካላት ጋር ሙሉ በሙሉ በመተባበር ይሰራል። ባለሥልጣኑ ከግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት
ሕክምና አገልግሎት ጋር በመተባበር ጃ ክሎችንና ቀበሮዎችን ከእብድ ውሻ በሽታ ለመከላከል በሚደረገዉ የክትባት በፕሮጀክቱ ላይ አጋር ነው። እንደ ፕሮጀክቱ አካል የእብድ ውሻ በሽታን የሚከላከሉ የአፍ ውስጥ ክትባቶች ከአውሮፕላኖች እና ከመሬት ውስጥ ይረጫሉ , ዓላማውም ጃካሎችን እና ቀበሮዎችን ለመከተብ ነው . እነዚህ እርምጃዎች ጠቃሚ ናቸው , ነገር ግን ውጤታማነታቸው የተገደበ ነው , እና ጃካሎች , ቀበሮዎች እና ሌሎች የዱር እንስሳት ክመጠን በላይ እንዳይበዙ ተጨማሪ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ።

ሁላችንም ተጽዕኖ ማድረግ የምንችለው ዋናው ነገር የም ግብ አቅርቦትን እና የሰውን ቆሻሻን መቆጣጠር እና በሰፈራ ውስጥ በሚገኙ የመመገ ቢያ ቦታዎች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ነው ።

ሁላችንም ልናደርጋቸው የምንችላቸው አንዳንድ ውጤታማ እና ቀላል ድርጊቶች እዚህ በታች ተጽፈዋል ።

በቀላሉ ምግብ የሚገኝባቸዉን ቦታዎች ማስወገድ :

ቆሻሻ ን ማስወገድ ፣ ወደ መጣያ ቦታ ዎች ውስጥ መጣል እና በጥብቅ መዘጋት አለበት። የሞቱ ደሮዎችን ፣ አሳ ዎችን እና የእንስሳት ሬሳ እንስሳት ከሚደርሱበት ቦታ ላይ መጣል የለበትም፣ ይልቁንም ወደ ተወሰነዉ ማጠራቀሚያ ኮንቴይነሮች መጣል አለበት ።

መከላከያ አጥር :

የ ደ ሮ እርባታ ቤቶች ፣ የቤት እንስሳት ቤቶች እንዲሁም የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን እና የምግብ ማእከሎችን በደንብ መታጠር አለባቸዉ ።

የቤት እንስሳትን ይጠብቁ :

የቤት እንስሳትዎ ብቻቸውን እንዲዘዋወሩ አይፍቀዱ። ከውሻው ጋር ሲ ወጡ ውሻዉ መታሰ ር አለበት . ውሾቹ ከእብድ ውሻ በሽታ መከላከያ መከተብ አለባቸው። የቤት ውስጥ እና የእርሻ እንስሳትን መከተብ የባለቤቶቻቸው ኃላፊነት ነው ።

በጥሩ ሁኔታ ይመግቡ :

የቤት እንስሳትን ምግብ ከቤት ውጭ በተከፈቱ ቦታዎች ላይ አይተዉት። እንሰሳትን በቀን እንጅ በምሽት አይመግቡ በምሽት የዱር አራዊት በሚንቀሳቀሱበት ሰዓት ነዉ የተረፈውን ምግብ ከውጪ መተው የለበትም .እንዲሁም የሳዳና ድመቶችን በኃላፊነት ስሜት መመገብ እና የተረፈውን ምግብ እና ውሃ መወገድ ሃላፊነት አለብን ።

ርቀትን ጠብ ቁ :

የዱር እንስሳትን መመገብ እና እነሱን መወዳጀት በባህሪያቸው ላይ ለውጥ ሊያመጣ እና በሰው ላይ ያላቸውን ተፈጥሯዊ ፍርሃት ሊቀንስ ይችላል። እነሱ ሲቀርቡን ከነሱ የመ ጎ ዳት አደጋን ያስከትልብናል ።

በማንኛውም ንክሻ ውስጥ የንክሻ ቦታው በብዙ ውሃ እና ሳሙና መታጠብ አለበት , አስቸኳይ ህክምና ይፈልጉ እና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሪፖርት ያድርጉ . በከተሞች ውስጥ የቤት እንስሳትን እና ዝግጅቶችን በተመለከተ ወደ ማዘጋጃ ቤት ወይም ምክር ቤት የእንስሳት ሕክምና አገልግሎት ቀጥታ ማነጋገር አለብዎት ። ንክሻው ከ ዱር አውሬ የመጣ ከሆነ ወይም ኃይለኛ የዱር አራዊት ካጋጠመዎት ወዲያውኑ *3639 በመደወል ለተፈጥሮ እና ፓርኮች መ/ቤት ባለስልጣን ያሳውቁ ።



